Radio Rainbow
ቀስተ ደመና ሬዲዮ
Radio Arc - En - Ciel
C/o P.O.Box 140 104. 53056 BONN. GERMANY - Fax: (49) 228 / 61 23 81

# ዓለም አቀፍ ሰብአዊ ምብቶች ድንጋጌ

## እያንዳንዱ አንቀጽ ምን ይላል ?

መጋቢት 1989

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
*Groupe de Recherche et d'Action pour la paix en Ethiopie et dans la Corne de l'Afrique*
*Research and Action Group for Peace in Ethiopia and the Horn of Africa*
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

ይህቺን አጭር ጽሁፍ ለማዘጋጀት ለተባበረን “የአውሮፓ ሰብአዊ
መብቶች ድርጅት (EUROPEAN FOUNDATION FOR
HUMANRIGHTS) ምስጋናችንን እናቀርባለን

## መግቢያ

ዛሬ የኢሕአዴግ መንግሥት በየአቅጣጫው የሰው ልጅ ምብትን ይረግጣል እየተባለ ነጋ ጠባ የሚወገዝ ስመ ጥሩ መንግሥት እየሆነ ሄዷል። በዓለም ላይ የሰው ልጅ መብት የሚረግጡ መንግሥታት ትላንትም ነበሩ ዛሬም አሉ። ታዲያ ይህ አገዛዝ ሌላው ቀርቶ ጠላት ተብለው በማይጠረጠሩ የውጭ ወዳጆች ሳይቀር ላላሰለሰ ውግዘትና እንደጉድ እየታየ ለመሄድ የበቃበት ምን ምክንያት የለ? በእኛ ግምት ለዚህ ክስተት ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ይታዩናል።

1ኛው ምክንያት በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው የመብት ረገጣ በዛሬው ዓለም ምንም ተወዳዳሪ የሌለው ሰፊ፣ የማያቋርጥና ከዕለት ዕለትም እየከፋ የሚሄድ ረገጣ መሆኑ ነው። ከኢትዮጵያ ዊው ኢሰመጉ እስከ አምኔስቲ ኢንተርናሽናል፣ ከዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች ማሕበራት እስከአሜሪካን ሰኔት አባላት፣ ከአውሮፓ ፓርትላሜንት እስከዓለም አቀፍ የሕግ ባለሙያዎች ኮሚሽን ... በአጠቃላይ በድፍን ዓለም የሰው ልጅ መብት ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት የሚስማሙበት አንድ ነገር አለ። ዛሬ በአገራችን በፖለቲካ ምክንያት ከ 10 ሺ ዜጎች በላይ በእስር የሚሰቃዩ ሲሆኑ ይህ ቁጥር በድፍን አፍሪካ በተመሳሳይ ሁኔታ የታሰሩ ዜጎች ቁጥር ቢደመር እንደማይደርስበት ተረጋግጧል።

2ኛው ምክንያት የኢህአዴግ የመብት ረገጣ በዛሬይቱ ዓለም በመንፈስ ላይ ካለው የዴሞክራሲያዊ ለውጥ አውሎ ነፋስ ጨርሶ የሚጻረር ሂደት መሆኑ ነው። ዛሬ ሌላውን ሁሉ ትተን በአፍሪካችን እንኳን ብንወሰን፣ ከዕለት ዕለት ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄድ አገሮች ዴሞክራሲን እየተላበሱ ሲሄዱ እናያለን። ከዚህ አጠቃላይ የአፍሪካ አሕጉር በጎ ሂደት አንፃር ሲታይ የኢሕአዴግን መሪዎች በብዙ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ዘንድ እጅግ ኋላ ቀርና አሻቅብ ለምፍሰስ እንደሚሞክር ውሃ አስመስሏቸዋል።

3ኛው ምክንያት ይህ ልክ ያጣ የመብት ረገጣ ራሱ ኢሕአዴግ አምን በታለሁ ከሚለውና የውጭ ደጋፊዎቹም የትብብራችን መሠረቶቻችን ናቸው ከሚሏቸው የሰው ልጅ መብትን አስመልክተው ከተፈረሙ ዓለም አቀፍ ውሎችና አዋጆች በየዕለቱ በግልጽ የሚጋጭ ሂደት መሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ በሚባለውና በሚሠራው መካከል ያለው ቅራኔ በየዕልቱ እየ

ከፋና እየሰፋ እንደሚሄድ፤ በዚሁ ልክ ደግሞ ኢሕአዴግ ለወዳጅም ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነ እንደሚመጣ ከወዲሁ መገንዘብ አስቸጋሪ አይደለም።

ኢሕአዴግ በሕዝብ ዘንድ ምንም ተቀባይነት የሌለው ሃይል እንደመሆኑ መጠን ይህ የመብት ረገጣው ሂደት እየከፋ እንጂ እየለዘበ አይሄድም። በዚያው ልክ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ መወቀሱ እየጨ መረ ይሄዳል። ግን ደግሞ ይህ ወገዛ ብቻውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት አያረጋግጥለትም። እራሱ የዚህ ግፍ ሰለባ የሆነው ሕዝብ ተንቀሳቅሶ ለድፍን ዓለም ሕዝቦች በመድረስ ላይ ያለው ለኔም የማይደርስበት የተለየ እርግማን የለብኝም ብሎ ለምብቱ መንቀሳቀስ አለበት።

ይህም ትግል ሊሰምር የሚችለው ሕዝቡ መብቱን ጠንቅቆ አውቆ ሲነሳ ብቻ ነው። በመሆኑም በዚች አጭር ጽሁፍ የዛሬ 50 ዓመት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያወጣውን “ዓለም አቀፍ የስብአዊ መብቶች ድንጋጌ” ሙሉ ቃል እያንዳንዱ አንቀጽ ምን እንደሚል ከሚያብራራ ማስታወሻ ጋር እናቀርባለን።

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ሃያ አንድ አንቀጾች በአብዛኛው መልክ ከሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች እንዲሁም ከግለሰቦች ነጻነትና ግለሰባዊ ደህንነት ጋር የተቆራኙ ናቸው።

## አንቀጽ ፩

የሰው ልጆች ሁሉ ሲወለዱ ነፃና በክብርም በመብ ብቶችም እኩል ናቸው። የማሰብ ክፉና በጎን የመ ለየት ችሎታን የተላበሱ በመሆ ናቸው እርስ በርሳ በቸው በወንድማማችነት መንፈስ ሊተያዩ ይገባል

ሰዎች ነፃ ሆነው ተወልደዋል ሲባል፤ ለነፃነት እኩል መብት አላቸው ማለት ነው። ሆኖም ግን በኢኮኖሚ፤ በሶሻል፤ በሲቭልና በፖለቲካ ገደቦች ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ሲነኩ ይስተዋላሉ። ነፃነት በምንም ሁኔታ ምሉዕ መሆን ካለመቻሉም ሌላ፤ የአንዱ ሰው ነፃ ነት የሌላው ነፃነት ማጣት መሆንም አይቻለውም። ስለዚህ ነፃነት ከሥርዓተ አልበኝነት ጋር ፈጽሞ ሊመሳሰል አይችልም።

እኩልነት ማለት ደግሞ ሰዎች ሁሉ በአካል፤ በአእምሮ ጥልቀት፤ በተፈጥሮ ችሎታና በመሳሰሉት ባህርያት ተመሳሳይ ናቸው ማለት አይደለም። እርግጥ ግለሰቦች የተለያዩ ናቸው። በማንኛውም የሶሻልና ባሕላዊ ስብስብ ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦች መካከል ያለው ልዩነት፤ በተለ ያዩ የሶሲዮና ባህላዊ ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች ካላቸው ለዩነት ጋር ሲነጻጸር፤ የፊተኛው የላቀ ሊሆን ይችልል። በብልህነት፤ በባህል ምጡቅነት፤ ወይም በዘር ጥራት አንዱን ሕብረተሰብ ክፍል ከሌላው አስበልጦ ማስቀመጥ የሚቻልበት አሳማኝ ምክንያት የለም። በዘር ሐረግ ወይም በፀረ ሕብረተሰብ ዕምነት የተነሳ በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ወይም ዘሮች ላይ የሚደረግ መድለዎ ምንም ዓይነት ሳይንሳዊ መሠረት የለውም። ከማንኛ ውም የሕብረተስብ ክፍል የፈለቁ ግለሰቦች፤ እንደሰውነታቸው የየተፈጥሮ ችሎታቸውን እንዳያዳብሩ ዕድል መንፈግ አሰቃቂ ግፍ ከመሆኑም በላይ፤ ለክብራቸውና ለመብታቸው ያላቸውን ዕኩልነት መንፈግ ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው በዕኩልነት እንዲመ ዘን ካስፈለገ፤ እያንዳንዱ ግለሰብ ሌላውን ሰው በወንድ ማማችነት መንፈስ እነዲመለከት ይህ አንቀጽ ያሳስባል።

## አንቀጽ ፪

ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በሕብረተሰብ ወይም ማሕበራዊ ምንጭ፣ በሐብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ ሁኔታ ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩ ነት ሳይደረግበት በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች ተጠቃሚ ነው።

በተጨማሪም የአንድ ሰው ሐገር ወይም የሚኖርበት ግዛት ነፃ፣ የአደራ ግዛት፣ እራሱን በራሱ የማያስተዳድር ግዛት ወይም በሉአላዊነቱ ሌላ ማንኛውም ገደብ የተደረገበት ሆነም አልሆነም በሐገሩ ወይም በሚኖርበት ግዛት የፖለቲካ ሥልጣን ወይም ዓለም አቀፍ አቋም ምክንያት ልዩነት አይደረግም፣

## አንቀጽ ፫

ማንኛውም ሰው የሕልውና፣ የነጻነትና የሰብእናው ደኅንነት የመጠበቅ መብት አለው።

ምንም እንኳን ይህንን የሰው ልጆች መብት ማስከበር የእያንዳንዱ ሐገር መንግሥት ተግባር ቢሆንም፣ በዓለማችን ላይ የሚገኙ በርካታ መንግሥታት ይህንን መብት ሲጥሱ ይስተዋላል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ብቻ በቁጥጥር ስር ውለው የተገደሉና ደብዛቸው ጠፍቶ የተሰወሩ ሰዎች ለመኖራቸው የማያሻሙ ማስረጃዎች ይገኛሉ። ሰዎች ሕገወጥ በሆነ መንገድ እንደሚገደሉ፣ እንደሚታፈኑና የት እንደደረሱ እንደማይታወቅ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በየጊዜው ዘገባዎችን ያወጣል። በዚህ ዓይነት ሕገወጥ መንገድ ሰለባ ስለሚሆኑ ሰዎች ቁጥር እየቀነሰ ለመምጣቱ የተገኘ መረጃ የለም። የሰቆቃ ምርመራን አክሎ፣ ይህን መሰል የሰብአዊ መብት ረገጣ የዓለም አቀፉን ሕብረተሰብ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ እያሳሰበው መጥቷል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች እንደሚታየው የመብቶች መጣስ የአንድን ብሔር፣ ጎሳ፣ ዘር ወይም የሃይማኖት ቡድን በአካል ወይም በሕሊና፣

በሙሉ ወይም በከፊል ለመደምሰስ የሚደረግን ሙከራ ያጠቃልላል። ይህ ዓይነቱ ሙከራ ደግሞ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው። የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመከላከልና ወንጀለኛን ለመቅጣት በወጣው ዓለም አቀፍ ሰነድ ላይ በማያወላውል ሁኔታ እንደተመለከተው የዘር ማጥፋት ወንጀል ዓለም አቀፍ ወንጀል ነው።

አንቀጽ ፬

ማንም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት አይያዝም።ባርነትና የባሪያ ንግድ በማናቸውም መልኩ ሁሉ የተከለከሉ ናቸው።

የዛሬውን ዘመን ባርነት በታሪክ እንደምናውቀው ሰዎች ተይዘው ና በካቴና ታስረው በግልጽ ገበያ የሚሸጡበት ዓይነት አይደለም። ይህ ዓይነቱ የባሪያ ንግድ ከረጅም ጊዜ በፊት ከመወገዱም ሌላ፣ በማንኛውም ሐገር ውስጥ ፍጹም የተከለከለ ነው። ሆኖም ግን አሁንም ቢሆን በበርካታ አገሮች የሚገኙ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የሰው በሰው ብዝበዛ ሰለባ ሆነው ይስተዋላሉ። የዛሬው ዘመን ባርነት ለሰው ልጆች የሚሰጠውን ክብር አለመቀበል ጋር ይዛሜዳል። በዓለም የኢኮኖሚና ሶሻል መዋቅር ሥር ሰደው የሚኖሩትን ድህነትን፣ መድልዎን፣ ድንቁርናን፣ ምቀኝነትንና መንገብገብን ለማስወገድ ከፍተኛ ችግር ጎልቶ ይታያል። ከባርነት ጋር የሚመሳሰሉ ግን በሌላ ስሞች የሚጠቀሱ እኪተ ተገባራት ደከም ያሉትንና የተጎዱ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ሲያውኩ ይታያሉ። ባርነትን፣ የባሪያ ንግድንና ከባርነት ጋር የሚመሳሰሉ ተግባራትን የሚያስፈጽሙ አካላትን ለማስወገድ በ 1956 እ.ኤ.አ. የወጣው ስምምነት ላይ በማያሻማ መንገድ የተቀመጡት፣ ጭሰኝነት፣ የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛና የጭን ገረድ ጋብቻ በቀጥታ የባሪያ ሥርዓት ሌላው ገጽታ ናቸው።

አንቀጽ ፭

ማንም ሰው የማሰቃየት ተግባር ወይም ጭካኔ የተመላበት ኢሰብአዊ የሆነ ወይም ክብረሕሊናን የሚነካ አድራጎት ወይም ቅጣት አይፈጸምበትም።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 10 ቀን 1984 በሙሉ ድምጽ ያጸደቀው መሰቃየ ትን፤ ወይም በጭካኔና ኢ-ሰብአዊ በሆነ መንገድ መጉላላትን ወይም መዋረድን ወይም መቅጣትን በሚከለክለው ዓለም አቀፍ ስምምነት ላይ በማያሻማ መንገድ ሰቆቃዊ ምርመመራና (ቶርቸርን) በሚከተለው መንገድ ይተረጉመ ዋል፤

"የሰቆቃ ምርመራ (ቶርቸር) ማለት ከአን ድሰው ወይም ከአንድ ከሌላ ሦስተኛ ሰው ላይ መረጃን ወይም የዕምነት ቃል ለማግኘት ሲባል አካላዊም ሆነ ህሊናዊ የሆነ ከፍተኛ ህመም፤ ስቃይን የሚያስከትል ሆን ተብሎ የሚፈጸም ድርጊት ነው። ወይም አንድ ሰው ወይም ሌላ ሦስተኛ ሰው ለፈጸመው ወይም ፈጽሟል ተብሎ በሚታሰብ ድርጊት ምክንያት በሚደረግ ቅጣት፤ ወይም ማስፈራራትና ማዋከብ፤ በመንግ ሥት ባለሥልጣን ወይም የመንግሥት ስልጣንን መከታ ባደረገ ግለሰብ ስምምነት ወይም ሴራ የተነሳ በማንኛውም ዓይነት መድልዎ ምክንያት ነት የሚፈጸም ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ይህም የሚያስከትለው ሕመምና ምከራ ነው።" እ.ኤ.አ. በ 1993 የወጣው የቪየና ድንጋጌና የድር ጊት መርሐ-ግብር የሰብአዊ ክብርን የሚረግጥና የሚጻረር ዋንኛው ኢ-ሰብ አዊ ድርጊት የሰቆቃ ምርመራ (ቶርቸር) መሆኑን ይደነግጋል።

የሰቆቃ ምርመራ (ቶርቸር) የመልክዐ ምድር ወሰን የለውም። ወይም የአንድ የተወሰነ ርእዩተ ዓለም ወይም የኢኮኖሚ ሥርዓት መግለጫ ባህርይም አይደለም። አምኔስቲ ኢንተር ናሽናልና ዓለም አቀፍ የዳኞች ኮሚሽን የመሳሰሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመላው ዓለም የተፈጸሙ በሺዎች የሚቆጠሩ የሰቆቃዊ ምርመራ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን በተጨባጭ ማስረጃ እያስደገፉ ያቀርባሉ። አንዳንድ መንግሥታት መረጃን ለማግኘት ወይም በሃይል ለማሳመንና አጠቃላዩን ሕብረተሰብ ለማስፈራራት የሰቆቃ ምርመራን (ቶርቸርን) ይጠቀማሉ።

ማንኛውም ዓይነት ሞራላዊም ሆነ ሕጋዊ ሁኔታ የሰቆቃ ምርመራን እንደማይቀበል ሁሉ፤ አብዛኛው ብሔራዊ ሆነ ዓለም አቀፍ ሕግ የሰቆቃ ምርመራን ይከለክላል የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 5 የሰቆቃ ምርመራን በመከልከሉ የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች በሙሉ ይህንን እንዲያከብሩ ይጠበቃል።

## አንቀጽ ፮

ማንም ሰው በየትኛውም ቦታ በሕግ ፊት እንደሰው የመታወቅና ተቀባይነት የማግኘት መብት አለው።

## አንቅጽ ፯

> ሰዎች ሁሉ በመካከላቸው ምንም ልዩነት ሳይደረግባ ባቸው በሕግ ፊት እኩል ናቸው።እኩል የሕግ ጥበቃም ይደረግ ላችዋል።

እነዚህ ሁለት አንቀጾች መድልዎን ለመከላከል የሚያስችሉትን ቀዳሚ መርሆች ይገልጻሉ። አንቀጽ 2 ድንጋጌውን ተግባራዊ በማድረግ በኩል ምንም ዓይነት መድልዎ እንዳይደረግ ያሳስባል። አንቀጽ 7 ደግሞ በአጠቃላይ መልኩ የአያንዳንዱ አገር ሕግ በሥራ ሲተረጎም መድልዎ አልባ እንዲሆን፤ ያረጋግጣል። በአንቀጽ 2 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ሁሉ የእያንዳንዱ ሐገር ሕግ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደ ረግ ጥበቃ እንዲያደረግ አንቀጽ 7 ሁሉንም አገሮች ይጠይቃል። በሕግ ፊት ሁሉም ሰው የሕግ ጥበቃ እንዲደረግለት ሕግ ተርጓሚ ባለሥልጣናት ሁሉ፤ ማለትም የፍትህ አካላትና ፖሊስ ሥርዓት የሚዘረጉበትን መንገድ እንዲሹ ይጠብቃል። ከዚህም በላይ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌን በመጣስ በአናሳ (ሕዳጣን) ሕዘቦች ላይ ምንም ዓይነት መድልዎ እንዳይደረግ መንግሥታት ሁሉ ሃላፊነት እንዳለባቸው፤ በአናሳ (ሕዳጣን) ላይ መድልዎ እንዲደረግ ማደፋፈር ሕገወጥ እንደሆነ አበክሮ ያስገነዝባል።

## አንቀጽ ፰

> ማንኛውም ሰው በሕገ መንግስት ወይም በሕግ የተሰጠውን መሠረታዊ መብቶቹን የሚጥሱ ድር ጊቶች በተፈጸሙበት ጊዜ ሥልጣን ባላቸው ብሔ ራዊ ፍርድ ቤቶች ዘላቂ መፍትሔ የማግኘት መብት አለው።

በዓለም አቀፍ ድንጋጌው አንቀጽ 6 ለሰብአዊ መብቶች ሕጋዊነት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጥ ነው። “በሕግ ፊት ሰው ሆኖ የመታወቅ” የሚለው ሐረግ ግለሰቦች የሚፈጽሟችው ውሎች፤ ኮንትራቶች ወዘተ. በሕግ ፊት የሚጸኑ ለመሆናቸው መንግሥታት ለዚህ የግለሰቦች መብት ዕውቅና እንዲሰጡና ይህም ምብታቸው በሕግ ፊት የተከበረ ለመሆኑ የሚያመለክት ነው።

በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰው "እያንዳንዱ ሰው የሚለው" ቃል በእጅጉ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ምንግሥት በማናቸውም ዜጎቹ መካከል፣ በውጭ አገር ሰዎች ወይም
በሐገረ የለሾች ላይ ምንም ዓይነት ልዩነት ወይም መድልዎ እንዳይደረግ ስለሚጠቅም ነው።

የአንቀጽ 8 ዋንኛ አላማ አንድ ግለሰብ በሕገመንግሥትም ሆነ በሌላ ሕግ የተሰጡት መሠረታዊ መብቶች የተጣሱ ናቸው በማለት የሚያምን ከሆነ ሥልጣን ላላቸው ፍርድ ቤቶች አመልክቶ መብቱን ልማስጠበቅ እንዲችል ነው። ይህ አንቀጽ ከዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ጋር የተጣቀሰ ሳይሆን፣ በሕገመንግሥትም ሆነ በሐገሩ ሌላ ሕጎች ላይ የተጠቀሱት መብቶች ላይ የተመለከተ ነው።

ይህም ማለት የአንዱ ወይም የአንዷ መብት በተጣሰ ጊዜ መብቱን ወይም መብቷን ለማስከበር የማይቻልበት ሁኔታ በፍጹም እንዳይፈጠር የሚያደርግ ይሆናል። ከዚህም በላይ "እያንዳንዱ ሰው" የሚለው ቃል እንዲሰፍር የተደረገው በሕገመንግሥትም ሆነ በሌላ ማናቸውም ሕግ ላይ የሰፈረው የግለሰቦች መብት ተጥሷል የሚል ዕም ነት አንድ ግለሰብ ካደረበት፣ ይህን መብቱንም ለማስከበር ስልጣን ላላ ቸው የሐገሩ ፍርድ ቤቶች የማመልከት መብቱ እንዳይጣስና ይህ የማመልከት ወይም የመክሰስ መብት ለተወሰኑ የሕበረተሰብ ክፍሎች ብቻ የተሰጠ መብት እንዳይሆን ለማድረግ ነው።

አንቀጽ ፱

> ማንም ሰው በሕገወጥ መንገድ እንዲያዝ፣
> በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ወይም እንዲጋዝ
> አይደረግም።

ይህ አንቀጽ ከዘፈቀደ እሥራት ነፃ እንዲሆንና ነፃና ትክክለኛ ፍትህ እንዲያገኝ የሚደረግበት እንዲሁም ካለተፈረደ በት በስተቀር ወንጀለኛ እንዳልሆነ የሚታወቅበትን መሠረታዊ የሕግ ከለላ የሚያገኝበትን መብት የሚያጎናጽፍ ነው።

የዚህ አንቀጽ ትርጉም ግልጽና የማያሻማ ነው። አንቀጹ በሁለት ዓይነት ይተረጎማል። አንደኛው ሰዎች በሕግ አግባብ ሊታሰሩ፣ ሊያዙ፣ ሊጋዙ ይችላሉ ሲሆን፣ ሁለተኛው ትርጉም ደግሞ ወንጀል ለመፈጸማቸው የሚያመለክት ማስረጃ ከሌለ በስተቀር ሰዎች ሊታሠሩ፣ ሊያዙም ሊጋዙ አይችሉም የሚል ነው።

የመጀመሪያው ትርጉም ደካማና የተዛባ ነው። ምክንያቱም ሕግ በራሱ የዘፈቀደና የማንአለብኝነት እርምጃ እንዲወሰድ ሥልጣን ያለው በመሆኑ ለሰው ልጆች ክብርና ነፃነት አስጊ ሁኔታን ይፈጥራል። በሆኑም የአንቀጹ ትክክለኛ አተረጓጎም ሁለተኛው ብቻ ነው። አንድ ሰው ጥፋተኛነቱ ካልተረጋገጠ በስተቀር ሊያዝ፤ ሊታሰር ወይም ሊጋዝ አይችልም።

አንቅጽ ፲

ማንኛውም ሰው በሚቀርብበት ማንኛውም የወንጀል ክስም ሆነ የመብቶቹንና የግዴታዎቹን አወሳሰን በሚመለከት ረገድ ጉዳዩ ነፃና አድልዎ በሌለበት ፍርድ ቤት በሙሉ እኩልነት ፍትህ ባለው ግልፅ ችሎት እንዲታይለት መብቱ የተጠበቀ ነው።

አንቀጽ 10 ትክክለኛና ነፃ የሆነ ፍትህ የሚገኝበትን መንገድ ወይም መብት ያመለክታል። አንቀጹ የሚመለከተው የወንጀል ጉዳዮችን ብቻ ሳይሆን፤ ፍትሐበሔርንም ይመለከታል።

ምንም እንኳን "ነፃ፤ ትክክለኛ" እና "አድልዎ የሌለበት" የሚለው ዕሳቤ ከሐገር ሐገር የሚለያይ ቢሆንም፤ እያንዳንዱ ሰው ጉዳዩን የማሰማት ዕድል እንዲኖረው ያስፈልጋል። በእያንዳንዱ ሐገር መንግሥታት የዳኝነት ነፃነት የሚባለው ነገር ተቀባይነት እንዲኖረው ያስፈልጋል።

አንቀጽ ፲፩

1. ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው እራሱን ለመከላከል የሚያስፈልጉት ዋስትናዎች ሁሉ በሚገባ በተረጋገጡበት ግልጽ ችሎት ቀርቦ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ መሠረት እስካልተወሰነ ድረስ ንጹህ ሰው ሆኖ የመገመት መብት አለው።

2. አድራጎቱ በተፈጸመበት ወቅት በብሔራዊ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ ሥር ወንጀልን በማያቋቁም ማንኛውም ድርጊት ወይም ግድፈት ምክንያት ማንም ሰው ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ እንደጥፋተኛ አይቆጠርም። እንዲሁም

ወንጀል በተፈጸምበት ወቅት በሥራ ላይ ካለው የበለጠ ቅጣትም አይወሰንበትም።

አንቀጽ 11 አራት መሠረታዊ መርሆችን ይዳስሳል።

<u>እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር</u> ይህ መርህ ቀላል ግን ደግሞ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ይህም ማለት አንድ ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በውል እስኪረጋገጥ ድረስ በወንጀለኛ ዓይን መታየት የለበትም ነው። በአንዳንድ ሐገሮች በፍርድ ሂደቱ ጊዜ በዋስ መብት ግለሰቦች ነፃነታቸው እንዲጠበቅ ይደረጋል።

<u>የመከላከል መብት</u>
አንቀጽ 11 ውስጥ የተመለከተው "ዋስትና" የሚለው ቃል፤ አንድ ሰው ወይም ሰዎች በአንድ ወንጀል ወይም በተለያዩ ወንጀሎች በተከሰሱ ጊዜ በጠበቃ የመረዳት፤ ንጽሕናቸውን ለማረጋገጥ እንዲችሉ ምስክሮችን የመጥራት መብታቸውን መንግሥታት እንዲያረጋግጡ የሚጠይቅ ነው።

<u>ግልጽ በሆነ ፍርድ ቤት</u>
በእንቀጽ 11 ውስጥ "ፍትሕ መገኘት አለበት ብቻ ሳይሆን፤ ፍትሕ ሲገኝም መታየት አለበት" የሚለው ብሒል ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል።
ሕዝቡ በሕግ ላይ እምነት እንዲኖረው የፍርድ ሂደት በግልጽ መከናወን አለበት።

<u>ሕግ ወደኋላ አይመለስም</u>
አንድ ሰው አንድ ተግባር ወንጀል ነው ተብሎ ባልተደነገገበት ግን በፈጸመው ተግባር ሊቀጣ አይገባውም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ከነበረው ቅጣት የበለጠ ሊወሰንበት አይችልም።

## አንቀጽ ፲፪

ማንም ሰው በግል ሕይወቱ፤ በቤተሰቡ፤ በመኖሪያ ቤቱ ወይም በሚያደርገው መጻጻፍ ሕገወጥ ጣልቃ ገብነት፤ እንዲሁም ክብሩንና መልካም ስሙን የሚያጎድፍ ጥቃት አይፈጸምበትም።

ማንኛውም ሰው ከእንዲህ ዓይነቱ ጣልቃ ገብነት ወይም ጥቃት የመጠበቅ መብት አለው።

### አንቀጽ ፲፫

1. ማንኛውም ሰው በእያናዳንዱ መንግሥት የግዛት ክልል ውስጥ ከቦታ ወደቦታ በነፃ የመዘዋወርና የመኖር መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ሐገር የራሱንም ጭምር ለቅቆ የመሄድና ወደሐገሩ የመመለስ መብት አለው።

### አንቀጽ ፲፬

1. ማንኛውም ሰው ከሚፈጸምበት ጥቃት ለመዳን በሌሎች ሐገሮች ጥገኝነት የመጠየቅና የመጠቀም መብት አለው።

2. በትክክል ፖለቲካ ነክ ባልሆኑ ወንጀሎች ወይም ከተባ በሩት መንግሥታት ዓላማዎችና መርሆች ጋር በሚቃረኑ ድርጊቶች ምክንያት የሚቀርቡ ክሶች ለማምለጥ ከሆነ ይህን መብት መጠየቅ አይችልም።

ጥገኝነት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከጥቃት ልማምለጥ ሲባል ወደሌሎች ሐገሮች የከበለሉ ስደተኞችንና ለነሱም የሚደረገውን ከለላ በሚመለከት ነው።

የጥገኝነት መብት በዓለም አቀፍ ደረጃ አልተደነገገም። በአሕጉር ደረጃ ያለው አንድ ሕግ የአሜሪካ ግዛቶች ድርጅት (Organization of Amercan States) ያወጡት ድንጋጌ ብቻ ነው። ሆኖም ግን ጥገኝነትን በተመለከተ ውሳኔው የእያንዳንዱ ሀገር መብት ሆኖ እስካሁን ቆይቷል። አንዳንድ ሐገሮች ይህንን አንቀጽ በጠባብ ትርጉሙ ሥራ ላይ ሲያውሉ ሌሎች ሐገሮች ደግሞ ሰፋ ባለ መልኩ በሥራ ይተረጉሙታል።

## አንቀጽ ፲፭

1. ማንኛውም ሰው ዜግነት የማግኘት መብት አለው።

2. ማንም ሰው በሕገ ወጥ መንገድ ዜግነቱን አይነጠቅም፤ እንዲሁም ዛግንቱን የመለወጥ መብቱንም አይነፈግም።

ዓለም አንድ ሀገር ሆኖ በዓለም አቀፍ ሕግ ሁሉም ሰው ዕኩል ቢሆን ኖሮ ዜግነት የሚባለው ነገር ትርጉም አልባ በሆነ ነበር። ይህ ስላልሆነ የግለሰቦችን የማቴሪያልና ሕሊናዊ ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ ዜግነት በእጅጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ዜግነት የግለሰቦች ማንነት መግለጫ ነው። በዚህ የተነሳ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 24 ለእያንዳንዱ ሕፃን ዜግነትን የሚያጎናጽፈው መብት ሰጥ ቷል። በዜግነት ጥያቄ ዙሪያ የፖለቲካ ልዩነትና ግጭት ተከስቶ እንመለከታለን። በቅርቡ በተከሰቱ የሃይል ግጭቶች ውስጥ ብሔርተኝ ነት ከዋነኛ መንስዔነት ይጠቀሳል። በቅርቡ ነፃነታቸውን ያወጁ ሐገሮች መመሥረት ከሕዝብ ጥቃትና ከሀገር መባረር ጋር በቀጥታ በመያያዝ የአገር አልባ ግለሰቦችን ቁጥር አበርክቷል ሕጻጣኖች ዋነኛ ሰለባዎች ናቸው።

እ.ኤ.አ. በ 1961 የፀደቀው የአገር አልባዎችን ቁጥር የመቀነስ ስምምነት፤ በአንድ አገር የግዛት ክልል ውስጥ የሚወለዱ ሕፃናት አገር አልባ እንዳይሆኑ ምንግሥታት የዜግነት መብት እንዲሰጡ ይደነግጋል። በምንም ዓይነት ሁኔታ በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጎሳ እና በፖለቲካ ምክንያት ማንም ሰው የዜግነት መብቱ ወይም መብቷ አይገፈፍም።

## አንቀጽ ፲፮

1. አካለመጠን የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በዜግነት ወይም በሃይማኖት ምክንያት ምንም ዓይነት ገደብ ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው። ጋብቻን በተመለከተ በጋብቻው ወቅትም ጋብቻው ሲፈጸም እኩል ምብት አላቸው።

2. ጋብቻ የተጋቢዎቹ ነፃና ሙሉ ፍላጎት ሲኖር ብቻ ይፈጸማል።

3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ አካል በመሆኑ በሕብረተሰቡና በመንግሥት ጥበቃ ይደረግለታል።

## አንቀጽ ፲፯

1. ማንም ሰው ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በማሕበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብት አለው።

2. ማንም ሰው በሕገወጥ መንገድ ንብረቱን

## አንቀጽ ፲፰

ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህም መብት ሃይማኖቱን ወይም ዕምነቱን የመለወጥና ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በሕብረት፣ በግልም ሆነ በይፋ ሃይማኖቱን ሆነ እምነቱን በማስተማር ተግባራዊ በማድረግ፣ በማምለክና በመከተል የማንጸባረቅን ነፃነት ይጨምራል።

የሃሳብ፣ የህሊናና፣ የሃይማኖት ነፃነትና መብት መሠረታዊ ነፃነት ከመሆናቸውም በላይ፣ በአስቸኳይ ጊዜያዊ አዋጅ ወቅት እንኳን ሊገደቡ አይችሉም። ለሃይማኖት ተከታዮች የሚሰጠው መብት ምንም ዓይነት ሃይማኖት ለማይከተሉትም በእኩልነት ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ማንም ሰው በዕምነቱ ምንም ዓይነት መድልዎ ሊደረግበት አይገባም ። ወይም የሌሎችን ዕምነት በግድ እንዲቀበልም አይገደድም።

አንዳንድ መንግሥታት በሃይማኖት ላይ ባላቸው አዝማሚያ የተነሳ በዚህ ነፃነት ስፋትና ጥበት የተለያየ ሆኖ ይታያል። አንዳንድ መንግሥታት አንድን ሃይማኖት ብቻ እየደገፉ ሌላውን ስለሚቃወሙ ሕዝብ አንድን የተወሰነ ሃይማኖት በሃ ይል እንዲቀበል ግፊት ያደርጋሉ።

የህሊና ነፃነትን በተመለከተ ብዙ ጊዜ አጨቃጫቂ ችግር ይነሳል። ይኸውም የአንድ ግለሰብ የህሊና ሁኔታ ከሚኖርበት ሕብረተሰብ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ አተረጓጎም ጋር የሚኖረው ዝምድና ነው።

ለዚህ ነፃነት አወዛጋቢ ግንዛቤ ቢኖርም በዚህ ረገድ መድለዎና አለመቻቻል እንዳይኖር እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 1981 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ማንኛውንም ዓይነት አለመቻቻልና መድልዎን ለማስወገድ በወጣው ድንጋጌ ላይ የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ለዚህ መብት ተጠባቢነት ተንፀባርቋል። ይህንን ድንጋጌ ተግባራዊ

ለማድረግ እ.ኤ.አ. 1986 የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ልዩ ሪፖርተር ሰይሞል። ይህ ሪፖርተር በ 1995 ካወጣው ሪፖርት ለመገንዘብ እንደሚቻለው በዓለማችን ላይ ከሚታወቁት ዕምነቶች ተከታዮች የሚሰነዘረው አስተያየት በርካታ ቅራኔዎችን ያዘለ ነው። ጽንፈኛና የጭፍን ጥላቻ አስተያየት ፕሮፓጋንዳንና የግለሰቦችን ህይወት ማጥፋት፣ ነፃነትንና ደህንነት ማጓደልን፣ እስራትንና ሰቆቃዊ ምርመራን አስከትሏል። የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በቅርቡ ባሳለፈው ውሳኔ ማንኛውንም ዓይነት ጥላቻ፣ አለመቻቻል፣ የአመጽ ተግባር የሃይማኖት ጽንፈኞችና የእምነት ተከታዮች ያለመቻቻል ተግባርን ሁሉ በጽኑ አውግዟል። ለማንኛውም ዓይነት የውትድርና አገልግሎት ግለሰቦች ላላቸው ህሊናዊ ዕምነተኝንት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዕውቅና ሰጥቷል። የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ውሳኔ 1993/94 የዓለም መንግሥታት በሙሉ ዜጎቻቸውን በብሄራዊ ውትድርና ለማሰልጠን ጫና እንዳያደርጉ ያሳስባል።

## አንቀጽ ፲፱

> ማንኛውም ሰው የአመለካከትና ሐሳቡንም በነፃ የመግለጽ መብት አለው። ይህ መብት ያለጣልቃ ገብነት የራስን አመለካከት የማራመድና ድንበር ሳያግደው በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ መረጃና ሐሳቦች የመጠየቅን፣ የመቀበልንና የማካፈልን ነፃነት ይጨምራል።

የእነዚህ መብቶች ጥበቃና ተግባራዊነት የአንድ ዴመክራሲያዊ ሕብረተሰብ የጀርባ አጥንት ነው። "በማናቸውም ዓይነት መንገድ መረጃዎችን፣ ሃሳቦችን የመፈለግና የማስተላለፍ" የሚለው ሐረግ የመገናኛ ብዙሐንን ነፃ መሆንን የግድ ያደርገዋል።

ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት መርገጥ የሚመነጨው ከፍርሃት ነው። ይህ ፍርሃት የሚመነጨው ሌሎች አማራጭ ሐሳቦችን እንደ ጦር በመፍራት ነው። ይህ ፍርሃት የሚመነጨው የግለሰቦችን መሠረታዊ ነፃነቶችን ደህንነት ማስጠበቂያው ዋነኛው መሳሪያ ሃሳብን በነፃነት መግለጽ ሲቻል እንደሆነ በመታወቁ ነው። ምንም እንኳን አንዳንድ መንግሥታት ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መርገጥ ቢችሉም፣ እስከወዲያኛው ነፃ አስተያየትንና ሃሳብን አፍነው ሊቆዩ አይቻላቸውም። መጽሐፍትን መከልከል ማለት መጻሕፍት ተደለዙ ማለት አይደለም። መጻሕፍት እንዳይታተሙ ማድረግ የእነዚህን መጻህፍት ሌላ ቦታ መታተምን፣ መሰራጨትንና መነበብን አያቆመውም።

ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብትንና የመገናኛ ብዙሕንን በነፃነት መንቀሳቀስ ለማረጋገጥ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተለያዩ ልዩ ልዩ ወኪል መስሪያ ቤቶቹ አማካይነት በርካታ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ሳይገደብ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም ይሁን በብሔራዊ ክልሎች የመረጃዎች ፍሰት በተመጣጠነ፣ በተሻለና በሰፋ ሁኔታ እንዲካሄድ ዩኔስኮ አዲስ የኮሙኒኬሽን ስራቴጂ ነድፎ ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛል። ዩኔስኮ በምሥራቅና በመካከለኛው አውሮፓ ሴሚናሮችን አዘጋጅቷል። (ፓሪስ 1989 እና 1990፣ አፍሪካ - ቪንድሁክ 1991፣ እስያ - አልማቲ 1992፣ ላቲን አሜሪካና ካሪቢያን - ሳንቲያጎ ዴ ቺሊ 1994፣ በአረብ አገሮች - ሰነዓ 1996) ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመሸጋገር ላይ ላሉ ሀገሮች የመገናኛ ብዙሃን ሕግ ሲቀረጽ የሙያ ምክር ይሰጣል። ይእርስ በርስ ግጭት ውስጥ በወደቁ ሐገሮች የመገናኛ ብዙሐን ወገነዊ ያልሆነ ዘገባ በማቅረብ ሰላምን የሚወልድ ውይይት እንዲደረግ ያግዛል። እ.ኤ.አ. በ 1993

የዩኔስኮ ልዩ ራፖርትር በመሰየም እነዚህ ምብቶች የሚጠበቁበትን ወይም የበለጠ እንክብካቤ የሚደረግበርትን ሁኔታ በመፍጠር ላይ ነው።

የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ሰነድ እንደሚያመለክተው ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ ምብት ለዩ ሃላፊንትና ግዴታዎችም አሉት። እነዚህም የሌሎችን መልካም ስም ማክበር፤ ብሔራዊ ደህንነትንና የሕብረተሰበ ሥርዓት፤ የሕዝብ ጤንነትና ሞራልን ከሚነካ ነገር መቆጠብ ናቸው። ማንኛውንም ዓይነት የጦርነት ቅሰቀሳ፤ መድለዎን፤ ጥላቻንና አመጽን የሚያስከትሉ የዘር፤ የብሔር፤ ወይም የሃይማኖት ጥላቻ ላይ በተመሠረቱ ማናቸውም ዓይነት ፕሮፓጋንዳ እንዳይካሄድ ሰነዱ ይከለክላል። በመሆኑም ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ፍጹም ሆኖ አይታይም።

አንቀጽ ፳

1. ማንኛውም ሰው ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግና በማሕበር የመደራጀት መብት አለው።

2. ማንም ሰው የአንድ ማሕበር አባል እንዲሆን ሊገደድ አይችልም።

ሰዎች በጋራ ዓላማቸውን ለመግለጽ፤ እንደቡድን ሆነው ጫና ለማድረግና ጥቅማቸውን፤ ወይም የሌሎችን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚችሉበት ዋንኛው መሳሪያ ማሕበር የማቋቋም ነፃነት ነው። ይህንን ነፃነት ለማስከበርም፤ ከመንግሥት ምንም ዓይነት ችሮታ አይጠበቅም። በሌላ በኩል ግን መንግሥታት ይህንን መብት ሊገድቡት ይችላሉ። ይህ ገደብ ሊደረግ የሚችልበት አንዳንድ ሕጋዊ ምክንያቶች እንዳሉ ቢታወቅም፤ በአብዛኛው ሁኔታ ግን ገደቡ የሚጣለው ለጭቆና ሲባል ነው። በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም የሚገኙ መንግሥታት ማሕበርን በነፃነት የመመስረት መብትን ሲረግጡ ይስተዋላሉ።

አንቀጽ ፳፩

1.ማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በነፃ በተመረጡ ተወካዮቹ አማካይነት በሐገሩ የመንግሥት አስተዳደር የመካፈል መብት አለው።

1.ማንኛውም ሰው በሐገሩ ውስጥ በመንግሥት ሥራ ለመቀጠር እኩል ዕድል የማግኘት መብት አለው።

1.የሕዝብ ፍላጎት የመንግሥት ሥልጣን መሠረት ይሆናል። ይህ ፍላጎት በምስጢር ድምፅ በመስጠት ሁሉም በእኩልነት በሚሳተፉባቸውና በየወቅቱ በሚደረጉ በሚደረጉ ትክክለኛ ምርጫዎች ወይም ተመሳሳይነት ባላቸው ድምፅ በነፃ በሚሰጥባቸው ሥነሥርዓቶች ይገለጻል።

የዴሞክራሲያዊ መንግሥት ዋነኛ መርህ የሆነው “የመንግሥት ሥልጣን መሠረቱ የሕዝብ ፈቃድ ነው።” የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ተግባራዊነት በዚህ አንቀጽ ውስጥ ተነጸባርቋል። ይህም ዕውን የሚሆነው በዕውነተኛ ምርጫ ብቻ ነው። ሐቀኛ ምርጫ ማለት ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ ነው። ነፃና ትክክለኛ ምርጫ ለዴሞክራሲው ሂደት መሠረት ሲሆን፤ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃና የሕግ የበላይነት አስፈላጊነት ሊታለፍ የማይችል ይሆናል። ትምሕርት ለሰብአዊ መብቶችና ትምሕርት ለዴሞክራሲን አጣምሮ የያዘው የሞንትሪያል የድርጊት ፕሮግራም የዴሞክራሲን የተቀደሰ ዓላማ አስፈላጊነት ለሰብአዊ መብቶች ጥበቃና፤ እንክብካቤ ነው በማለት በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጧል።

አንቀጽ ፳፪

ማንኛውም ሰው የሕብረተሰቡ አካል እንደመሆኑ መጠን የማህበራዊ ዋስትና መብት አለው። ስለሆነም በብሔራዊ ጥረትና በዓለም አቀፍ ትብብር አማካይነትእንደእያንዳንዱ መንግሥት ድርጅታዊ ብቃትና

የሐብት አቅም ለክብሩና ለሰብዕናው ዕድገት ወሳኝ የሆኑት የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባሕላዊ መብቶቹን ተግባራዊ የማስደረግ መብት አለው።

ይህ አንቀጽ እንዲሁም ከአንቀጽ 23 እስከ አንቀጽ 27 ያሉት አንቀጾች ሁሉ የሰው ልጅ ለክብሩና ለሰውነቱ ነፃ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑት ቁሳዊና ቁሳዊ ያልሆኑ ፍላጎቶች እንዲሟሉለት፣ በኢኮኖሚው፣ በሶሻልና በባህል መስኮች ረገድ ያሉት መብተቹ እንዲከበሩና እንዲጠበቁ ይደነግጋል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም የመንግሥታትና የዓለም አቀፉ ሕብረተሰበ ሙሉ ፈቃደኝነት ያሳፈልጋል።

አንድ አምሳል የሆነው የዓለም ሕዝብ በድህነትና በበሽታ ይሰቃያል፣ በሽታ፣ መሃይምነትና ሕብረተሰባዊ ሥጋት እየጨመሩ በመምጣት ላይ የሚገኙ ክስተቶች ናቸው። የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ የሲቭልና የፖለቲካ መብቶች ሲጣሱ፣ አምርሮ እንደሚቃወመው ሁሉ በዓለማችን ላይ ያለ ርህራሄ በመጣስ ላይ ላሉት መሠረታዊ የሶሻል፣ የኢኮኖሚና የባህል መብቶች መረጋገጥ ተመሳሳይ ጽኑ ተቃውሞ ማንሳት ይጠበቅበታል። የኢኮኖሚ፣ የሶሻል፣ የባህል የፖለቲካና የሲቭል መብቶች ነፃነት ሙሉ ዕውቅና እስካላገኘ ድረስ፣ ዴሞክራሲ መረጋጋትና ሰላም ዕውን ሊሆኑ አይቻላቸውም። ምንም እንኳን የኢኮኖሚ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ ቢሆንም፣ አጠቃላዩን የግለሰቦች የግለሰቦች ድህንነት ግን ሊያስከብር ከቶውንም አይቻለውም። የኢኮኖሚ ዕድገት ጥቅም በራሱ ለሁሉም ሕዝብ ተርታ የጥቅም ተቋዳሽነትን አያስከትልም። ስለሆነም የኢኮኖሚና የሾሻል ዕድገትን ለማረጋገጥ የሚደረግ ብሔራዊ ጥረትም ሆነ ዓለም አቀፍ ትብብር የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባህል መብቶች በአመርቂ ሁኔታ ተጠብቀው ከመገኘታቸው ጋር መቆራኘት ያሳፈልጋል።

## አንቀጽ ፳፫

1. ማንኛውም ሰው የመሥራት። የሚፈልገውን ሥራ በነፃ የመምረጥ፣ ተገቢና አመቺ የሥራ ሁኔ ታዎችን የማግኘትና ከሥራ አጥነት የመጠበቅ መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብት አለው. ማንኛውም የሚሠራ ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ እንደሰው ክብር ያለው ህልውና የሚያረጋግጥ፣ አግባብ ያለውና በቂ ክፍያ

3. ማንኛውም የሚሠራ ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ እንደሰው ክብር ያለው ህልውና የሚያረጋግጥ፣ አግባብ ያለውና በቂ ክፍያ የማግኘት፣ አስፈላጊም ከሆነ በሌላ የማሕበራዊ ዋስትና ዘዴዎች የመደጎም መብት አለው።

4. ማንኛውም ሰው ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ የሙያ ማህበራትን የማቋቋም፣ አባልም የመሆን መብት አለው።

### አንቀጽ ፳፬

ማንኛውም ሰው በአግባቡ የተወሰኑ የስራ ስዓቶችና በየወቅቱ ከክፍያ ጋር የሚሰጡትን የዕረፍት ቀናት ጨምሮ የማረፍና የመዝናናት መብት አለው።

### አንቀጽ ፳፭

1.ማንም ሰው ምግብን፣ ልብስነ መጠለያን የጤና እንክብካቤን እንደሁም አስፈላጊ የሆኑትን ማሕበራዊ አገልግሎቶች ጨመሮ ለራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደህንነት በቂ የሆነ የኒሮ ደረጃ መብት አለው። አንዲሁም በሥራ አጥነት፣ በህመም፣ በችሎታ ማጣት ቤል በሞተ፣ በእርጅና ወይም ከአቅም በላይ በሆኑ ሁኔታዎች ምክንያት ለሉሮው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች በጡ ጊዜ ዋስትና የማግኘት መብት አለው

2.እናትነትና ሕጻንነት ልዩ ጥንቃቄና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በጋብቻም ሆን ከጋብቻ ውጭ ቢወለዱ ለሁሉም ሕፃናት ተመሳሳይ ማህበራዊ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

አንቀጽ ፳፮

1.ማንኛውም ሰው ትምሕርት የማግኘት መብት አለው። ቢያንስ በአንደኛና በመዋዕለ ሕጻናት ደረጃዎች ትምሕርት በነፃ ይሆናል። የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ለሁሉም ግዴታ ይሆናል። የቴክኒክና የሞያ ትምሕርት በአጠቃላይ እንዲኖር ይደረጋል፤ እንዲሁም ችሎታን መሠረት በማድረግ የከፍተኛ ትምሕርት ዕድል እኩል ለሁሉም ይሰጣል።

2. ትምሕርት በሰው ልጅ ሰብእና ዕድገት መሟላትና ለሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች በሚሰጠው ክብር መጠናከር ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል። በሁሉም አገሮች የዘር ወይም የሃይማኖት ቡድኖች መካከል መግባባትን፤ መቻቻልንና ወዳጅነትን ያበረክታል። እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ሰላምን ለማስጠበቅ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ያዳብ ራል።

3.ወላጆች ለልጆቻቸው መሰጠት ያለበትን የትምሕርት ጥዕይነት የመምረጥ ቅድሚያ መብት አላቸው።

በተለያዩ አገሮች ለትምሕርት ዘርፍ የሚሰጡት ትኩረት በእጅጉ ይለያያል። በብዙ ሐገሮች መሠረታዊ ትምሕርት የሚከናወን ቢሆንም፤ በዓለም ላይ መሃይምነትን ልማጥፋት እስካሁን አልተቻለም። ከዓለም ሕዝብ ሩቡ ወይም ወደ አንድ ቢሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ መሃይምን ነው። ከድህነት፤ ከአድልዎና ከንፍገት የተነሳ በርካታ ሰዎች ለትምሕርት ያላቸው ቅርበት የራቀ በመሆኑ፤ የመማር መብት በብዙ ቦታ ተጥሶ ይስተዋላል።
ትምሕርት የመምረጥ መብት ከሕብረተአቡ ፍላጎት ጋር የግድ መቆራኘት ይሮርበታል። የዚህ ዓላማ ዕውን መሆን ግን ብዙ መንገድ ገና ይቀረዋል። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ነፃና የስፈላጊ ተብሎ

በሚታመንባቸው ሀገር እንኳን፣ ከትምሕርት ቤቶች አቀማመጥ ርቀት፣ ከፋይናንስ፣ ከቤተመጻሕፍትና ከትምሕርት አጋዥ ቁሳቁሶች አለመስተካከል፣ እንዲሁም ከመምሕራን ማሰልጠኛ ተቋማት ጥራት ማነስ የተነሳ በትምህርት ምርጫና ለትምሕርት ያለው ዕድል ይጨናገፋል።

በብዙ ሐገሮች የከፍተኛ ትምሕርት በነፃ አይሰጥም። የነፃ ትምሕርት ዕድል፣ የአዋቂዎች ትምሕርት፣ ወይም በሥራ ላይ ሥልጠና ከፍተኛ ትምሕርት የሚገኙባቸው ሌሎች መንገዶች ናቸው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘው በትምሕርት ሰፊና ዘላቂ አላማ የሰውን ልጅ የተሟላ ዕድገት ለማራመድና የሰብአዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን ለማክበር እንዲያግዝ ማድረግ ነው። የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ መግቢያ "እያንዳንዱ ግለሰብም ሆነ የሕብረተሰብ ክፍል ... ለእንዚህ መብቶችና ነፃነቶች መከበር በመማርና በማስተማር ሂደት ማገዝ ይገባዋል" በማለት ጥሪ ያደርጋል

በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አካላት አማካይነት ትምሕርት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ባህል እንዲጳብርና በዕውቀትና በሙያ በመታገዝ የባህርይ ለውጥ እንዲመጣ በሚከተሉት ላይ ማተኮር ይገባዋል።

ሀ. ሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች እንዲከበሩና እንዲጠናከሩ፣

ለ. የሰው ልጆችን ሰብአዊ ክብርና ዕድገት ለማራመድ፣

ሐ. በመግባባት፣ በሕዝቦች፣ በተለያዩ ዘሮችና በሃይማኖቶች መካከል መቻቻልንና ወንድማማችንትን ለማቤረ ታታት

መ. ሁሉም ሰዎች በሕብረተሰባቸው ውስጥ በበቂ ሁኔታ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማገዝ፣

ሠ. በተባበሩት መንግሥታት ለሰላም ጥበቃ የሚያደርገውን ትግል ለመደገፍ።

እነዚህ ዓላማዎች በመደበኛ ትምሕርትም ሆነ መደበኛ ያልሆነ ትምሕርት በሚሰጥባቸው ሥፍራዎች ሁሉ፣ መንፀባረቅ ይኖርባቸዋል። የተባበሩት መንግሥ ታት ድርጅት የትምሕርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እ.ኤ.አ. በ 1974 ያወጣው "ትምሕርት ለዓለም አቀፍ መግባባት ትብብርና ሰላም" እንዲሁም "ትምሕርት ለሰብአዊ መብቶችና

መሰረታዊ ነፃነቶች" የሚሉት መርሃ ግብሮች፤ ከዚህ በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በ 1979 የሰብአዊ መብቶችን ትምሕርት ለማራመድ የነደፋቸው መርሃ ግብር በበርካታ መንገዶች በሥራ በመተርጎም ላይ ነው።

አንቀጽ ፳፯

1.ማንኛውም ሰው በሕብረተሰቡ የባህል ሕይወት ውስጥ በነፃ የመሳተፍ፤ በሥነ ጥበብ የመጠቀም፤ በሳይንስ ዕድገትና በሚሰጠውም ጥቅም የመካፈል መብት አለው።

2.ማንኛው ም ሰው ከሳይንስ፤ ከሥነ ጽሁፍና ከስነ ጥበብ ሥራዎች የተገኙትን መንፈሳዊና ቁሳዊ ጥቅሞቹን የማስጠበቅ መብት አለው።

ይህንን አንቀጽ በሚመለከት ዩኔስኮ እ.ኤ.አ. በ 1974 እና በ 1976 ባወ ጣቸው ሰነዶች አቋሙን ግልጽ የድርጓል ። የባህል መብት አንድ ሰው የራሱንም ሆነ የሌሎችን ባሕላዊ እሴቶችን የማወቅ መብቱን ያጠቃልላል። በባህል ኑሮ በነፃነት የመሳተፍ ማለት በድራማ፤ ሙዚቃ፤ በባህላዊ ጭፈራና በባህላዊ የሙዚቃ ድግሶች ውስጥ መሳተፍ መቻልን ይጨምራል። የባህል መብት ማለት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መጠቀም መቻል ነው። ባጠቃላይ አነጋገር ይህ መብት የመማር መብት ማለት ነው፤ እንደሌሎች የሰብአዊ መብቶች ሁሉ የባህል መብት በሕግ ደረጃ በሕግ ደረጃ በተገቢው መንገድ አለመቀመጡን ማጤንና መገንዘብ ያስፈልጋል።

አንቀጽ ፳፰

ማንኛውም ሰው በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተደነገጉት መብቶችና ነፃነቶች ሙሉ በሙሉ በተግባር በሚተረጎሙበት ማህበራዊና ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት ውስጥ የመኖር መብት አለው።

ለበርከት ላሉ አሥርቶች ዓለም አቀፍ ጥረቶች በዕድገት ላይ ያተኮረ ቢሆንም፤ በዓለም አቀፍም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ በድሃና በሐብታም መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ከመሄድ አልታቀበም። ይህ የሚያመለክተው የዓለም ሃብት ፍትሐዊ ያልሆነ ክፍፍል በሥራ ላይ በሚውሉ ፖሊሲዎችና ተቋማት እየተደገፈና እየተጠናከረ መሄዱን ነው። የኢኮኖሚ ዕድገት በራሱ እንደ ግብ መታየት አይገባውም። የኢኮኖሚ እድገት ትርጉም ያለው ዕድገት አጋዥ ሆኖ በሰዎች ሙሉ ክብርና ዕድ ገት ላይ መመስረት አለበት።

ታዳጊ አገሮች በኢኮኖሚ ጥገኝነት ተቀፍድደው ይታያሉ። የዕድ ገት አለመመጣ ጠንን ለማስተካከል አዲስ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስር ዓት እንዲዋቀርና ከውጭ ዕዳ ቀንበር መላቀቅ እንዳለባቸው ተገንዝቦም ያደጉት አገሮች ይህንን ለመገንዘብ ዳተኝነት ያሳያሉ። በዕድገት የላቁት ሐገሮች ለሰላም፤ ለደህንነትና ለሰብአዊነት ያላቸው የረጅም ጊዜ ጥቅም በስራ ላይ በሚገኘው የኢኮኖሚ ሥርዓት ለውጥ ጋር በቀጥታ የተቆራኘ መሆኑን ተስኗቸዋል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ. በ 1986 ያወጣው የዕድገት መብት ድንጋጌ የዕድገት መብት የሰው ልጆች የማይገሰስ መብት እንደሆነ በትክክል አስቀምጦታል የ 1993 ቱ የቪ ዬና የተግባር መርሃ ግብር መግለጫ ይህንኑ አረጋግጧል። ኮፐንሐግን

ላይ ከማርች 6 -12 . 1995 የተሰበሰቡት የሕብረተስብ ዕድገት የመሪ ዎች ጉባዔም ባወጣው መግለጫ ይኸው ሃሳብ በበለጠ ተብራርቷል።

አንቀጽ ፳፱

1.ማንም ሰው ሰብዕናው ነፃና የተሟላ ዕድገት ሊያገኝ ለሚችልበት ብቸኛ ማዕከል ለሆነው ማሕበረሰብ ግዴታዎች አሉበት።

2.በማንኛውም ሰው የመብቶችና የነፃነቶች አጠቃቀም ላይ ሌሎች መብቶችና ነፃነቶች ተገቢውን ክብርና ተቀባይነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ዲሞክራሲ በሰፈነበት ሕብረተሰብ ውስጥ ደግሞ መልካም ሥነምግባርን፤ የሕዝብ ጸጥታንና አጠቃላይ ደህንነትን ለማስጠበቅ ሲባል ብቻ ገደቦች ይደረጉበታል።

3.እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች በምንም ዓይነት ቢሆን ከተባበሩት መንግሥታት ዓላማዎችና መርሆች ጋር በሚቃረን ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውሉም።

የሰብአዊ መብቶችን በማክበር ረገድ ዓለም አቀፍ ድንጋጌው ለዘረዘራቸው መብቶች ቅድሚያ በመስጠት በኩል ችግር እንደገጠማቸው በርካታ መንግሥታት ይከራከራሉ። በርግጥም ቀላል መልስ ሊገኝ ከቶውንም አይችልም። በመብቶች መካከል የእርስ በርስ ተቃርኖ እንዳል
እንዳለመኖሩ የሲቭል፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባሕል መብቶች አንዱ በሌላው ላይ የተመረኮዘና የተቆራኘ ነው። የኢኮኖሚ፣ የሶሻልና የባህል መብት መረጋገጥ ለማንኛውም ዓይነት ሕብረተሰባዊ ፍትህ ዕውን መሆን የማይታለፍ ይሆናል። ሁሉም ሰዎች ፍርሃት አልባ ነፃነት የሚያገኙበት ዋነኛውና ብቸኛው መንገድ እያንዳንዱ ሰው የኢኮኖሚ፣ የሶሻል፣ የባህልና እንዲሁም የሲቪልና የፖለቲካ መብቶቹ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ሲመቻች እንደሆነ ዓለም አቀፉ ድንጋጌ ያረጋግጣል።

የሰብአዊ መብቶች መሠረታዊ ነፃነቶች ዓለም አቀፋዊነት ፣ አለመነጣጠላቸው፣ ቁርኝታቸውና ዘምድናቸው እ.ኤ.አ. በ 1993 በወጣው የቪዬና የተግባር መርሃ ግብር መግለጫ ላይ በድጋሚ ተረጋግጧል። ይኸው መርሃ ግብር ዓለም አቀፉ ሕብረተ ሰብ በዓለም ደረጃ ሰብዓዊ መብቶችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንክብካቤ እንዲያደርጉ አበክሮ ያስገነዝባል።

ማንም ሰው ሰብአዊ መብቱ የሚከበረው፣ የተሟላ ሰብአዊ ዕድገቱ የሚረጋገጠው በሕብረተሰቡ ውስጥ በመኖሩ ብቻ ስለሆነና ማንም ሰው በራሱ መብቶችና ነፃነቶች በሚጠቀም ጊዜ የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ማወቅና ማክበር ግዴታው ነው። አንድ ሰው ሰብአዊ መብቶቹን በሚጠቀም ጊዜ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገው መሰረት መንግሥታት ገደብ ሊያበጁ ይችላሉ። ይህ ማለት ግን ዓለም አቀፉ ድንጋጌ ተግባራዊ እንዳይሆን ገደብ የመጣል ሕጋዊ መብት አላቸው ማለት እንዳልሆነ መጤን አለበት። የዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ሕጎች በሙሉ ሰብአዊ መብትና መሰረታዊ ነፃነቶች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ የሚፈጥሩ መሆን አለባቸው። ከዚህም በላይ ፍርድ ቤቶችና የፍትህ አካላት በሙሉ በሰብአዊ መብትና በመሰረታዊ ነፃነቶች ላይ የሚጣለው ሕጋዊ እቀባ አሳማኝ ለሆኑ ምክንያቶች መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው

### አንቀጽ ፴

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ማንኛውም መንግሥት፣ ቡድን ወይም ሰው በውስጡ የተደነገጉትን ማንኛውንም ምብቶችና ነጻነቶች ለማጥፋት በተቃታ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሰማራ ወይም ማንኛውንም ድርጊት እንዲፈጽም መብት የሚሰጥ ነው ተብሎ ምንም ነገር መተርጎም የለበትም።

ይህ ማለት ድንጋጌው በምንም ዓይነት ሁኔታ ሰብአዊ መብቶች ለመጣስ መገልገያ መሆን አይችልም ማለት ነው። ይህ ሕግ የሚጸናው ለመንግሥታት ብቻ ሳይሆን፣ ለግለሰቦችና ለቡድኖችም ጭምር ነው። ስለሆነም የዚህን ድንጋጌ አንድ አንቀጽ ብቻ ነጥሎ በማውጣት ሌሎች አንቀጾችን ወይም አንቀጽን ለመጣስ መጠቀም በፍጹም የተከለከለ ነው።

ድንጋጌው በተለይም በመጨረሻው አንቀጽ 30 አንድ ሰው የራሱንም ሆነ የሌሎችን መብት ለማስከበር በቆራጥነት እንዲነሳ ጥሪ ያቀርባል ይህ ቆራጥነትና ጀግንነት ሁሉም የሰው ልጆች ሰብአዊ መብታቸው በንድፈ - ሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን፣ በተግባር እንዲጠበቅ ለምናደርገው ትግል የሚከፈል ከፍተኛ ዋጋ ነው።

# ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ

# የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ አዋጅ

(እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 10.1948 በተባበሩት መንግሥታት ጠ.ጉባዔ ውሳኔ 2170 [iii] የጸደቀ)

## መቅድም

የሁሉም የሰው ልጆች የተፈጥሮ ክብር፤ እኩልና የማይገሰሱ መብቶች ማወቅና መቀበል በዓለም ላይ የነፃነት፤ የፍትሕና የሰላም መሠረት ስለሆነ፤

የሰብአዊ መብቶች ቸል መባልና መናቅ የሰው ልጅ ኅሊና ያቆሰሉ አረመኔያዊ ድርጊቶችን ስላስከተሉ፤ ዓለማችን የሰው ልጆች የንግግርና የእምነት ነፃነታቸው ተከብሮ ከድህት፤ ከረሃብና ከእርዛት ነፃ ሆነው የሚኖ-ሩበት እንድትሆን የሰፊው ሕዝብ ከፍተኛው ምኞት መሆኑ መገለጹ፤

የሰው ልጅ አምባገነንትንና ጭቆናን በመቃወም እንደመጨ ረሻ አማራጭ አድርጎ ወደአመጽ ለማምራት እንዳይገደድ ከተፈለገ የሰብአዊ መብቶቹ በሕግ የበላይነት ሥር መጠበቅ ወሳኝ በመሆኑ፤

በሐገሮች መካከል የወዳጅነት ግንኙነቶች እየዳበሩ እንዲሄዱ ማበረታታት አስፈላጊ ስለሆነ፤

የተባበሩት መንግሥታት ሕዝቦች በመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች፤ በሰው ልጅ ክቡርነትና ጠቃሚነት እንዲሁም በወንዶችና በሴቶች እኩል መብቶች ያላቸውን መብት በቻርተሩ ውስጥ እነደገና ስላረጋገጡና ማሕበራዊ ዕድገትና የተሻለ

የሕይወት ደረጃዎችን የበለጠ ነፃነት ባለው ሁኔታ ለማበረታታት ቁርጠኛ ስለሆኑ፤

አባል መንግሥታት ከተባበሩት መንግሥታት ጋር በመተባበር ሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት

እንዲያገኙና እንዲከበሩ የሚደረገው ማበረታታት ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ቃል ኪዳን የገቡ ስለሆነ፤
በእነዚህ ምብቶችና ነፃነቶች ላይ የጋራ ግንዛቤ መኖር ይህን ቃል ኪዳን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፤

ስለዚህ አሁን፤

ጠቅላላ ጉባዔው

በዚያው በአባል መንግሥታት ሕዝቦች መካከልና በእነሱ ሥልጣን ሥር በሚ ገኙ ግዛቶች ውስጥ ባሉ ሕዝቦች ምካከል በማስተማርና በማስልጠን ለእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ተገቢው ክብር እንዲሰጥ ለማበረታታትና እየጸ በሩ በሚሄዱ በሔራዊና ዓለም አቀፍ እርምጃዎች ውጤት ያለው ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ማግኘታቸውንና መከበራቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ግለሰብና እያንዳንዱ የሕብረተሰብ ተቋም ጥረት እንዲያደርግ በሚል አላማ ለሁሉም ሕዝቦችና መንግሥታት የውጤት የጋራ መለኪያ እንዲሆን ይህን የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ድንጋጌ ያውጃል።

## አንቀጽ ፩

የሰው ልጆች ሁሉ ሲወለዱ ነፃና በክብርም በመብቶችም እኩል ናቸው። የማሰብ ክፉና በጎን የመለየት

ችሎታን የተላበሱ በመሆናቸው እርስ በርሳቸው በወንድማማችነት መንፈስ ሊተያዩ ይገባል።

## አንቀጽ ፪

ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በፖለ ቲካ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በሕብረተሰብ ወይም ማሕበራዊ ምንጭ፣ በሐብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ ሁኔታ ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች ተጠቃሚ ነው።

በተጨማሪም የአንድ ሰው ሐገር ወይም የሚኖርበት ግዛት ነፃ፣ የአደራ ግዛት፣ እራሱን በራሱ የማያስተዳድር ግዛት ወይም በሉአላዊ ነቱ ሌላ ማንኛውም ገደብ የተደረገበት ሆነም አልሆነም በሐገሩ ወይም በሚኖርበት ግዛት የፖለቲካ ሥልጣን ወይም ዓለም አቀፍ አቋም ምክንያት ልዩነት አይደረግም፡

## አንቀጽ ፫

ማንኛውም ሰው የሕልውና፣ የነጻነትና የሰብእናው ደኅንነት የመጠበቅ መብት አለው።

## አንቀጽ ፬

ማንም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት አይያዝም። ባርነትና የባሪያ ንግድ በማናቸውም መልኩ ሁሉየተከለከሉናቸው።

## አንቀጽ ፭

ማንም ሰው የማሰቃየት ተግባር ወይም ጭካኔ የተመላበት ኢሰብአዊ የሆነ ወይም ክብረሕሊናን የሚነካ አድራጎት ወይም ቅጣት አይፈጸምበትም።

## አንቀጽ ፮

ማንም ሰው በየትኛውም ቦታ በሕግ ፊት እንደሰው የመታወቅና ተቀባይነት የማግኘት መብት አለው።

## አንቅጽ ፯

ሰዎች ሁሉ በመካከላቸው ምንም ልዩነት ሳይ-ደረግባቸው በሕግ ፊት እኩል ናቸው። እኩል የሕግ ጥበቃም ይደረግላቸዋል።

## አንቀጽ ፰

ማንኛውም ሰው በሕገ መንግስት ወይም በሕግ የተሰጠውን መሠረታዊ መብቶቹን የሚጥሱ ድርጊቶች በተፈጸሙበት ጊዜ ሥልጣን ባላቸው ብሔራዊ ፍርድ ቤቶች ዘላቂ መፍትሔ የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ ፱

ማንም ሰው በሕገወጥ መንገድ እንዲያዝ፣ በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ወይም እንዲጋዝ አይደረግም።

## አንቅጽ ፲

ማንኛውም ሰው በሚቀርብበት ማንኛውም የወንጀል ክስም ሆነ የመብቶቹንና የግዴታዎቹን አወሳሰን በሚመ-ለከት ረገድ ጉዳዩ ነፃና አድልዎ በሌለበት ፍርድ ቤት በሙሉ እኩልነት ፍትህ ባለው ግልፅ ችሎት እንዲታይለት መብቱ የተጠበቀ ነው።

## አንቀጽ ፲፩

1. ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው እራሱን ለመከላከል የሚያስፈልጉት ዋስትናዎች ሁሉ በሚገባ በተረጋገጡበት ግልጽ ችሎት

ቀርቦ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ መሠረት እስካልተወሰነ ድረስ ንጹህ ሰው ሆኖ የመገመት መብት አለው።

2. አድራጎቱ በተፈጸመበት ወቅት በብሔራዊ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ ሥር ወንጀልን በማያቋቁም ማንኛውም ድርጊት ወይም ግድፈት ምክንያት ማንም ሰው ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ እንደጥፋተኛ አይቆጠርም።

እንዲሁም ወንጀል በተፈጸምበት ወቅት በሥራ ላይ ካለው የበለጠ ቅጣትም አይወሰንበትም።

## አንቀጽ ፲፪

ማንም ሰው በግል ሕይወቱ፤ በቤተሰቡ፤ በመኖሪያ ቤቱ ወይም በሚያደርገው መጻጻፍ ሕገወጥ ጣልቃ ገብነት፤ እንዲሁም ክብሩንና መልካም ስሙን የሚያጎድፍ ጥቃት አይፈጸምበትም። ማንኛውም ሰው ከእንዲህ ዓይነቱ ጣልቃ ገብነት ወይም ጥቃት የመጠበቅ መብት አለው።

## አንቀጽ ፲፫

1. ማንኛውም ሰው በእያንዳንዱ መንግሥት የግዛት ክልል ውስጥ ከቦታ ወደቦታ በነፃ የመዘዋወርና የመኖር መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ሐገር የራሱንም ጭምር ለቅቆ የመሄድና ወደሐገሩ የመመለስ መብት አለው።

## አንቀጽ ፲፬

1. ማንኛውም ሰው ከሚፈጸምበት ጥቃት ለመዳን በሌሎች ሐገሮች ጥገኝነት የመጠየቅና የመጠቀም መብት አለው።

2. በትክክል ፖለቲካ ነክ ባልሆኑ ወንጀሎች ወይም ከተባበሩት መንግሥታት ዓላማዎችና መርሆች ጋር በሚቃረኑ ድርጊቶች ምክንያት የሚቀርቡ ክሶች ለማምለጥ ከሆነ ይህን መብት መጠየቅ አይችልም።

## አንቀጽ ፲፭

1. ማንኛውም ሰው ዜግነት የማግኘት መብት አለው።

2. ማንም ሰው በሕገ ወጥ መንገድ ዜግነቱን አይነጠቅም፤ እንዲሁም ዛግንቱን የመለወጥ መብቱንም አይነፈግም።

## አንቀጽ ፲፮

1. አካለመጠን የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፤ በዜግነት ወይም በሃይማኖት ምክንያት ምንም ዓይነት ገደብ ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው። ጋብቻን በተመለከተ በጋብቻው ወቅትም ጋብቻው ሲፈጸም እኩል ምብት አላቸው።

2. ጋብቻ የተጋቢዎቹ ነፃና ሙሉ ፍላጎት ሲኖር ብቻ ይፈጸማል።

3. ቤተሰብ የሕብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ አካል በመሆኑ በሕብረተሰቡና በመንግሥት ጥበቃ ይደረ-ግለታል።

## አንቀጽ ፲፯

1. ማንም ሰው ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በማሕበር የንብ ረት ባለቤት የመሆን መብት አለው።

2. ማንም ሰው በሕገወጥ መንገድ ንብረቱን አይነጠቅም።

## አንቀጽ ፲፰

ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የሃይማኖት ነፃነት አለው። ይህም መብት ሃይማኖቱን ወይም ዕምነቱን የመለወጥና ብቻውንም ሆነ

ከሌሎች ጋር በሕብረት፣ በግልም ሆነ በይፋ ሃይማኖቱን ሆነ እምነቱን በማስተማር ተግባራዊ በማድረግ፣ በማምለ-ክና በመከተል የማንጸባረቅን ነፃነት ይጨምራል።

## አንቀጽ ፲፱

ማንኛውም ሰው የአመለካከትና ሐሳቡንም በነፃ የመግለጽ መብት አለው። ይህ መብት ያለጣልቃገብነት የራስን አመለካከት የማራመድና ድንበር ሳያግደው በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ መረጃና ሐሳቦች የመጠየቅን፣ የመቀበልንና የማካፈልን ነፃነት ይጨምራል።

## አንቀጽ ፳

1. ማንኛውም ሰው ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግና በማሕበር የመደራጀት መብት አለው።

2. ማንም ሰው የአንድ ማሕበር አባል እንዲሆን ሊገደድ አይችልም።

## አንቀጽ ፳፩

1. ማንኛውም ሰው በቀጥታ ወይም በነፃ በተመረጡ ተወካዮቹ አማካይነት በሐገሩ የመንግሥት አስተዳደር የመካፈል መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው በሐገሩ ውስጥ በመንግሥት ሥራ ለመቀጠር እኩል ዕድል የማግኘት መብት አለው።

3. የሕዝብ ፍላጎት የመንግሥት ሥልጣን መሠረት ይሆናል። ይህ ፍላጎት በምስጢር ድምፅ በመስጠት ሁሉም በእኩልነት በሚሳተፉባቸውና በየወቅቱ በሚደረጉ ትክክለኛ ምርጫዎች ወይም ተመሳሳይነት ባላቸው ድምፅ በነፃ በሚሰጥባቸው ሥነሥርዓቶች ይገለጻል።

## አንቀጽ ፳፪

ማንኛውም ሰው የሕብረተሰቡ አካል እንደመሆኑ መጠን የማህበራዊ ዋስትና መብት አለው። ስለሆነም በብሔራዊ ጥረትና በዓለም አቀፍ ትብብር አማካይነት እንደእያንዳንዱ መንግሥት ድርጅታዊ ብቃትና የሐብት አቅም ለክብሩና ለሰብዕናው ዕድገት ወሳኝ የሆኑት የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባሕላዊ መብቶቹን ተግባራዊ የማስደረግ መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፫

1. ማንኛውም ሰው የመሥራት። የሚፈልገውን ሥራ በነፃ የመምረጥ፣ ተገቢና አመቺ የሥራ ሁኔታዎችን

X_________________________________________

የማግኘትና ከሥራ አጥነት ችግር የመጠበቅ መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብት አለው።

3. ማንኛውም የሚሠራ ሰው ለራሱና ለቤተሰቡ እንደሰው ክብር ያለው ህልውና የሚያረጋግጥ፣ አግባብ ያለውና በቂ ክፍያ የማግኘት፣ አስፈላጊም ከሆነ በሌላ የማሕበራዊ ዋስትና ዘዴዎች የመደጎም መብት አለው።

4. ማንኛውም ሰው ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ የሙያ ማህበራትን የማቋቋም፣ አባልም የመሆን መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፬

ማንኛውም ሰው በአግባቡ የተወሰኑ የስራ ሰዓቶችና በየወቅቱ ከክፍያ ጋር የሚሰጡትን የዕረፍት ቀናት ጨምሮ የማረፍና የመዝናናት መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፭

1. ማንም ሰው ምግብን፣ ልብስነ መጠለያንና የጤና እንክብካቤን እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑትን ማህበራዊ አገልግሎቶች ጨምሮ ለራሱና

ለቤተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ብቁ የሆነ የኑሮ ደረጃ መብት አለው። እንዲሁም በሥራ አጥነት፤ በህመም፤ በችሎታ ማጣት ባል በሞተ፤ በእርጅና ወይም ከአቅም በላይ በሆኑ ሁኔታዎች ምክንያት ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች በታጡ ጊዜ ዋስትና የማግኘት መብት አለው።

2. እናትነትና ሕጻንነት ልዩ ጥንቃቄና እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ ቢወለዱ ለሁሉም ሕፃናት ተመሳሳይ ማህበራዊ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

## አንቀጽ ፳፮

1. ማንኛውም ሰው ትምሕርት የማግኘት መብት አለው። ቢያንስ በአንደኛና በመዋዕለ ሕጻናት ደረጃዎች ትምሕርት በነፃ ይሆናል። የአንደኛ ደረጃ ትምሕርት ለሁሉም ግዴታ ይሆናል። የቴክኒክና የሞያ ትምሕርት በአጠቃላይ እንዲኖር ይደረጋል፤ እንዲሁም ችሎታን መሠረት በማድረግ የከፍተኛ ትምሕርት ዕድል እኩል ለሁሉም ይሰጣል።

2. ትምሕርት በሰው ልጅ ሰብእና ዕድገት መሟላትና ለሰብአዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች በሚሰጠው ክብር መጠናከር ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል። በሁሉም አገሮች የዘር ወይም የሃይማኖት ቡድኖች መካከል መግባባትን፤ መቻቻልንና ወዳጅነትን ያበረክታል። እንዲሁም የተባበሩት መንግሥታት ሰላምን ለማስጠበቅ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ያዳብራል።

3. ወላጆች ለልጆቻቸው መሰጠት ያለበትን የት-ምሕርት ጥዕይነት የመምረጥ ቅድሚያ መብት አላቸው።

## አንቀጽ ፳፯

1. ማንኛውም ሰው በሕብረተሰቡ የባህል ሕይወት ውስጥ በነፃ የመሳተፍ፣ በሥነ ጥበብ የመጠቀም፣ በሳይንስ ዕድገትና በሚሰጠውም ጥቅም የመካፈል መብት አለው።

2. ማንኛው ም ሰው ከሳይንስ፣ ከሥነ ጽሁፍና ከስነ ጥበብ ሥራዎች የተገኙትን መንፈሳዊና ቁሳዊ ጥቅሞቹን የማስጠበቅ መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፰

ማንኛውም ሰው በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተደነገጉትት መብቶችና ነፃነቶች ሙሉ በሙሉ በተግባር በሚተረጎሙበት ማህበራዊና ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት ውስጥ የመኖር መብት አለው።

## አንቀጽ ፳፱

1. ማንም ሰው ሰብዕናው ነፃና የተሟላ ዕድገት ሊያገኝ ለሚችልበት ብቸኛ ማዕከል ለሆነው ማሕበረሰብ ግዴታዎች አሉበት።

2. በማንኛውም ሰው የመብቶችና የነፃነቶች አጠቃቀም ላይ ሌሎች መብቶችና ነፃነቶች ተገቢውን ክብርና ተቀባይነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ እንዲሁም ዲሞክራሲ በሰፈነበት ሕብረተሰብ ውስጥ ደግሞ መልካም ሥነምግባርን፣ የሕዝብ ጸጥታንና አጠቃላይ ደህንነትን ለማስጠበቅ ሲባል ብቻ ገደቦች ይደረጉበታል።

3. እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች በምንም ዓይነት ቢሆን ከተባበሩት መንግሥታት ዓላማዎችና መርሆች ጋር በሚቃረን ሁኔታ ጥቅም ላይ አይውሉም።

## አንቀጽ ፴

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ማንኛውም መንግሥት፣ ቡድን ወይም ሰው በውስጡ የተደነገጉትን ማንኛውንም ምብቶችና ነጻነቶች ለማጥፋት በተቃታ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሰማራ ወይም ማንኛውንም ድርጊት እንዲፈጽም መብት የሚሰጥ ነው ተብሎ ምንም ነገር መተርጎም የለበትም።